1. ከሚከተሉት ወንጌላውያን ከ72ቱ አርድእት የሚመደበው የትኛው ነው?
ሀ) ማቴዎስ ለ) ማርቆስ ሐ) ሉቃስ መ) ለ እና ሐ

2. ቅዱስ ማርቆስ በዋናነት ወንጌል ያስተማረው በየት ነው?
ሀ) እስክንድርያ ለ) ኢየሩሳሌም ሐ) ደማስቆ መ) ህንድ

3. ቅዱስ ማርቆስ መጀመሪያ ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር ያስተማረው በየት ነው?
ሀ) እስክንድርያ ለ) ጵንፍልያ ሐ) እየሩሳሌም መ) ኢትዮጵያ

4. ከአራቱ ወቅቶች ቅዱስ ማርቆስ በየትኛው ይመሰላል? ምክንያቱስ ምንድን ነው?
ሀ) ጸደይ፤ የዘርን ምሳሌ ከሁሉ አምልቶ ስለጻፈ
ለ) መጸው፤ በነፋስ አምሳል መንፈስ ቅዱስ እንደሚሰጥ ተናግሯልና
ሐ) በጋ፤ መስተጻርርና መስተቃርን የሌለበት ደረቅ ቃል በመጀመሪያ ቃል ነበር... እያለ ጽፏልና
መ) ክረምት፤ ወንጌሉን በጌታችን ጥምቀት ይጀምራልና

5. የቅዱስ ማርቆስ ትውልዱ እና አስተዳደጉ በየት ነው?
ሀ) በኢየሩሳሌም ተወልዶ በኢየሩሳሌም አደገ
ለ) በቤተልሔም ተወልዶ በግብጽ አደገ
ሐ) በሰሜን አፍሪካ ሲሪኒካ(ቃሬና) ተወልዶ በኢየሩሳሌም አደገ
መ) በገሊላ ተወልዶ በዛው አደገ

6. የቅዱስ ማርቆስ እናት ማን ትባላለች?
ሀ) ማርያም ቀልዮጳ ለ) ማርያም ባውፍሊያ ሐ) ቬሮኒካ መ) መልሱ የለም

7. ቅዱስ ማርቆስ ወንጌሉን በዮሐንስ ጥምቀት የጀመረበት ምክንያት ምንድን ነው?
ሀ) በሮማውያን ባሕል መሠረት ንጉሥ ሲመጣ አጋፋሪው ከፊት ይቀድማልና እርሱም የንጉሥን መምጣት እያወጀ ያልፋል
ለ) ከሌሎቹ ወንጌላት ለየት ለማድረግ ብቻ
ሐ) መጥምቁ ዮሐንስ ዘመዱ ስለነበረ
መ) ሁሉም

8. ከወንጌላት ሁሉ አጭሩ የቱ ነው?
ሀ) የማቴዎስ ወንጌል ለ) የማርቆስ ወንጌል ሐ) የሉቃስ ወንጌል መ) የዮሐንስ ወንጌል

9. የቅዱስ ማርቆስ ወንጌል መጀመሪያ የተጻፈው በምን ቋንቋ ነበር?
ሀ) በአብራይስጥ ለ) በሮማይስጥ ሐ) በጽርዕ መ) በግእዝ

10. ከሚከተሉት ሐሰት የሆነው?
ሀ) ሰው ለሰንበት ተፈጥሯል
ለ) ሰንበት ለሰው ልጅ ተፈጥራለች
ሐ) ሰንበት በፈለግን ጊዜ የምንሽራት ናት
መ) ሀ እና ሐ

11. ከሐዋርያት ውስጥ የቅዱስ ማርቆስ ዘመድ የሆነው የቱ ነው?
ሀ) ቅዱስ ዮሐንስ ለ) ቅዱስ ጴጥሮስ ሐ) ቅዱስ ማቴዎስ መ) ከእነርሱ መካከል ዘመዱ የነበረ የለም

12. ከወንጌላውያን መካከል የመጀመሪያውን ወንጌል የጻፈው ማን ነው?
ሀ) ቅዱስ ማቴዎስ ለ) ቅዱስ ማርቆስ ሐ) ቅዱስ ሉቃስ መ) ቅዱስ ዮሐንስ

13. በቤተክርስቲያናችን አስተምህሮ መሠረት ቅዱስ ማርቆስ በአንበሳ የሚመሰልበት ምክንያት የቱ ነው?
ሀ) አራዊት የአንበሳን ጻሕር ሲሰሙ እንደሚደነግጡ ሁሉ ከአምልኮተ እግዚአብሔር ተለይታ በነበረቸው ግብፅ ወንጌልን ባስተማረ ጊዜ ኢጋንንትና መናፍቃን ደንግጠዋልና
ለ) አንበሳ ለላም ጌታው እንደሆነና እንደሚሰብረው ሁሉ ማርቆስም ከግብጽ ምድር በትምህርተ ወንጌል በላም ቅርጽ ሰርተው የሚያመልኩትን ጣኦት አጥፍቷልና
ሐ) በእስክንድሪያ ወንጌል ለማስተማር ሲዘዋወር ከአንበሶች ጋር ያታግሉት ነበርና
መ) ሁሉም መልስ ናቸው

14. የማርቆስ ወንጌል ስንት ምዕራፎች አሉት?
ሀ) 12 ለ) 16 ሐ) 20 መ) 25

15. የቅዱስ ማርቆስ እለተ እረፍቱ የሚታሰበው መቼ ነው?
ሀ) ሚያዚያ 30 ለ) መጋቢት 30 ሐ) ጎዳር 30 መ) መስከረም 30

16. የቅዱስ ማርቆስ ወንጌል ለአረማውያን መጻፉ በምን ይታያል?
ሀ)የአረማይክን ቃላትና የዕብራውያን ባሕልን ተርጉሞ በማስቀመጡ
ለ) ሮማውያን ኃያላን እንደሆኑ ስለሚያስቡ ከእነርሱ በላይ ኃያል እንዳለ ለማሳየት የጌታን ኃያልነት አጉልቶ በመጻፉ
ሐ) ስለ ጣዖታት በዝርዝር በማስቀመጡ
መ) ሀ እና ለ

17. የቅዱስ ማርቆስ አባት ማን ይባላል?
ሀ) በርናባስ ለ) አርስጦቡሎስ ሐ) ቅዱስ ባስልዮስ መ) መልሱ የለም

18. ቅዱስ ማርቆስ እና ቤተሰቦቹ ከሚታወቁበት መካከል ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ) ቅዱስ ማርቆስ ጌታ በቀራንዮ ሳለ እርቃኑን በነጠላ ሸፍኖ ይከተለው ነበር፣ በኋላም አይሁድ ሊይዙት ቢያስቡ ራቁቱን ሸሽቷል
ለ) በበዓለ ሃምሳ መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት የወረደላቸው በቅዱስ ማርቆስ እናት ቤት ነበር
ሐ) በምሴተ ሐሙስ ሐዋርያት ፋሲካን እንዲያዘጋጁ የተመረጠውን ቤት የጠቆማቸው ቅዱስ ማርቆስ ነበር
መ) ቅዱስ ማርቆስ ሳይሞት በብሔረ ሕያዋን እስካሁን አለ

19. ከቅዱስ ማርቆስ ቀድመው በግብጽ ለማስተማር የሞከሩ ነቢያት ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው?
ሀ) ኤርምያስ ለ) ሙሴ ሐ) ካህኑ ዘካርያስ መ) ሀ እና ሐ

20. ቅዱስ ማርቆስ ሰማዕትነትን የተቀበለው እንዴት ነው?
ሀ) ቁልቁል በመስቀል ተሰቅሎ
ለ) በሠረገላ አሥረው መንገድ ለመንገድ በመጎተት
ሐ) አንገቱን በመሰየፍ
መ) በእሳት በመቃጠል